*“ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተፀነስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ፤ ድንግል ሆይ በኃጢአት ፍትወት የተፀነስሽ አይደለም፣ በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐናና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ”*

**ቅዳሴ ሕርያቆስ**

## *የተከበራችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የድንግል ማርያም ወዳጆች!*

## *እንኳን ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የኦስተን ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስትያን ድህረ ገፅ በሰላም መጣችሁ !!*

*እንኳን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የልደት መታሰቢያ በዓል (ለግንቦት ልደታ ለማርያም) በሰላም በጤና አደረሳችሁ! ያለንበት ዘመን በእግዚአብሔር ጥባቆት በማስተዋልና በጥበብ የምንራመድበት ጊዜ ነው። በመሆኑም ዘንድሮ የእመቤታችንን የግንቦት ልደታ ለማርያምን አመታዊ የንግሥ ክብረ በዓል ማክበር ባንችልም የጸሎተ ቅዳሴውን እና የእለቱን ትምህርት በቀጥታ እየተከታተልን ከድንግል ማርያም ልደት በረከት ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ስም ለማስታወስ እንወዳለን።*

*የሰው ልጅ አርቆ ቢያስብም እግዚአብሔር የፈቀደው ነውና የሚሆነው የአስተዳደር ጽሕፈት ቤታችን በእቅዱ መሰረት ሊሰራ ያሰባቸውን ከመስራት ቢስተጓጎልም እንኳ እንደ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ በተቻለው ሁሉ ለአባላቶቻችን እና ለልደታ ወዳጆች ተደራሽ ለመሆን የቤተ ክርስቲያኗን ድህረ-ገጽ (Website) ያዘጋጀን በመሆኑ እየገባችሁ እንድትጎበኙት፣ የሚያስፈልጋችሁን አገልግሎት ለመጠየቅም ይሁን አስተዋጽዖ እና የአባልነት መባዎችን ለመክፈል የሚቻል መሆኑንም ለማሳወቅ እንወዳለን።*

**በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የኦስተን ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት!**